## ስለTESS ማዕከል

የ TESS ማዕከል በሞንትጎምሪ ካውንቲ የማህበረሰብ አገልግሎት የካውንቲውን የዝቅተኛ ገቢ ነዋሪዎች ፍላጎት ለማሟላት የተቋቋመ ማዕከል ነው። የ TESS ማዕከል በ DHHS ቦታ የሚገኝ የመንግስትን እና የግል ድርጅቶችን እርዳታና አገልግሎት ለሚፈልጉ ነዋሪዎች መረጃ የሚሰጥ እና መምራት የሚያካሄድ ያለቀጠሮ የሚገቡበት ቦታ ነው። ባለሁለት ቋንቋ ተናጋሪ (እንግሊዝኛ፣ እና ስፓኒሽ ወይም አማርኛ)የሆኑ ሰራተኞች እና የነጻ አገልግሎት ሰጪዎች ያሉበት፣ የሌላ ቋንቋ ተናጋሪዎችን ጨምሮ ሰፊ ስብጥር ያለው ማህበረሰብን ያገለግላሉ። እንደ አካባቢያዊ እድል ግንኙነት (NON) ቦታ፣ የማህበረሰብ አገናኞች እና NON አጋሮች የ TESS ሰራተኞችን ለነዋሪዎች አገልግሎት እንዲሰጡ በመርዳት ያግዛሉ። የሞንትጎምሪ ካውንቲ ነዋሪዎች እንደ ምግብ እና የተመጣጠነ ምግብ ፣ የህጻናት እንክብካቤ፣የመኖሪያ ቤት፣ እና የድንገተኛ ድጋፍ አገልግሎቶችን የመሳሰሉ አንገብጋቢ ፍላጎቶችን ለማሟላት ከእርዳታ ሰጪ ጋር ይገናኛሉ። TESS ከ 8,000 በላይ ደንበኞችን በየአመቱ ያገለግላል።

www.mc311.com

*መረጃው በተለያየ መልክ ይገኛል።*
*ትብብር ካስፈለግዎት፣ አባክዎትን በ 240-773-8260 ይደውሉ።*

ለመጨረሻ ጊዜ የተከለሰ: ጥር 2016

የጤና እና የሰብአዊ አገልግሎት ክፍል

*ኢሳያህ ሌጌት*
*የካውንቲ ሃላፊ*

*ኡማ ኤስ. አህሉዋሊያ*
*ዳይሬክተር*

# TESS ማዕከል

## *ታኮማ-ኢስት ሲልቨር ስፕሪንግ*
## የማህበረሰብ አገልግሎት ማዕከል

የኮሙኒቲ አክሽን ኤጀንሲ ፕሮግራም
እና የአካባቢያዊ እድል ግንኙነት ቦታ

8513 Piney Branch Road
Silver Spring MD 20901

**240-773-8260 (ዋና)**
**301-565-5713 (ፋክስ)**

መስማት ለተሳናቸው: 301-251-4850 ሜሪላንድ መስማት ለተሳናቸው: 711

**የስራ ሰዓት: ሰኞ - አርብ፣ 9 AM – 3 PM**
ያለ ቀጠሮ: 9 AM – 11 PM
በቀጠሮ: 1 PM – 3 PM

# TESS የማህበረሰብ አገልግሎት ማዕከል አላማዎች:

*ለካውንቲው ነዋሪዎች አገልግሎቶች እና እርዳታዎችን በማቅረብም ሆነ በማገናኘት ድህነትን መቀነስ፣ በራስ መተዳደርን መጨመር እና ማበረታታት።*

---

## በ TESS ማዕከል የሚቀርቡ አገልግሎቶች

- **መረጃዎች እና መምራቶች፥** የመንግስት እና የኮሙኒቲ ፕሮግራሞች እና ሃብቶች፣ ለምግብ፣ ለልብስ፣ ለጥርስ እና የጠቅላላ ጤና አገልግሎት፣ የህዝብ እና የግል ጥቅማ ጥቅሞች ማመልከቻዎችን፣ የመራጮች ምዝገባ እና የኖታሪ አገልግሎትን የተመለከቱ መረጃዎችን ያጠቃልላል።

- **የነጻ አገልግሎት የገቢ ግብር እርዳታ (VITA) አጋርነት:** ስለ "EITC" እና ሌሎች የግብር ታሳቢዎችን በማስተማር እና የግብር መልስ በትክክል መሞላቱን የሚያረጋግጥ ነጻ የግብር ወይም የታክስ ዝግጅት አገልግሎት ያቀርባል። (ከጃኑዋሪ መጨረሻ እስከ ኦክቶበር) 240-777-1123

- **ፕሮ ቦኖ ፕሮግራም** (Pro Bono): ከሞንትጎምሪ ካውንቲ የህግ ድርጅት ፕሮ ቦኖ ፕሮግራም ያሉ የነጻ አገልግሎት ጠበቆች ለሲቪል ጉዳዮች ነጻ የህግ የምክር አገልግሎት ይሰጣሉ። የማጣሪያ መጠይቆች ይኖራሉ። አገልግሎቱ በወሩ የመጀመሪያው እና ሶስተኛው ረቡዕ ላይ ይሰጣል።
  ምዝገባ: 6pm -7pm 301-424-7651/ 301-424-7652

- **የጁዲ ማዕከል (Judy center):** የመማር መጫወት (Play-literacy) ቡድኖች የህጻናትን የትምህርት ዝግጁነት ያሻሽላሉ። አገልግሎቱ ማክሰኞ እና ሐሙስ 10:00 – 11:30am ይሰጣል። 301-230-0691

- **የአዛውንቶች ማህበራዊ ቡድን**: ወርሃዊ የአዛውንቶች ፕሮግራም ተጋባዥ እንግዶችን፣ ገለጻዎችን፣ እና ልዩ ክንውኖችን ያካትታል። አገልግሎቱ በወሩ የመጨረሻው አርብ ላይ 11am – 1pm ይሰጣል።

- **የESOL ትምህርቶች**: ከ IMPACT Silver Spring ጋር በመተባበር፣ የ TESS ማዕከል የ ESOL ትምህርቶችን ለጀማሪዎች እና መሃከለኛ ደረጃ እንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች ያቀርባል። 301-298-5117

- **የበጋ ምግቦችን**: ከሞንትጎምሪ ካውንቲ የህዝብ ትምህርት ቤቶች ጋር በመተባበር፣ TESS እንደ በጋ ምግቦች ቦታ ያገለግላል፤ ትምህርት ቤት በሚዘጋበት የበጋ ወራቶች ለህጻናት ከ1,300 በላይ ነጻ ምሳዎችን ያቀርባል።

- **የበዓል ስጦታዎች:** እንደካውንቲው የበዓል ስጦታዎች ማስተባበሪያ አካል፣ ቤተሰቦች ፣ምግብ፣ መጫወቻዎች፣ ካፖርቶች እና የቤተሰብ እርዳታዎች ወደሚያደርጉ የማህበረሰብ ስፖንሰሮች እና አጋሮች ይመራል። የ "ቤተሰብ ይታደጉ" ፕሮግራም የማህበረሰቡ አባሎች በካውንቲው ላሉ ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው ቤተሰቦች የበዓል ስጦታዎች እንዲገዙ ይፈቅዳል።

- **በአጋሮቻችን የሚቀርቡ አገልግሎቶች:** የ Mary Center፣ CHEER፣ እና DHHS ፕሮግራሞች፣ የአረጋውያን እና የአካል ጉዳተኞች አገልግሎትን፣ የላቲኖ ጤና መምሪያ፣ እና የገቢ እርዳታዎችን ይጨምራል።